IB DIPLOMA PROGRAMME
PROGRAMME DU DIPLÔME DU BI
PROGRAMA DEL DIPLOMA DEL BI

22060014

**AMHARIC A1 – HIGHER LEVEL – PAPER 2**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU SUPÉRIEUR – ÉPREUVE 2**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL SUPERIOR – PRUEBA 2**

Tuesday 23 May 2006 (afternoon)
Mardi 23 mai 2006 (après-midi)
Martes 23 de mayo de 2006 (tarde)

2 hours / 2 heures / 2 horas

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Answer one essay question only. You must base your answer on at least two of the Part 3 works you have studied. You may include in your answer a discussion of a Part 2 work of the same genre if relevant. Answers which are not based on a discussion of at least two Part 3 works will not score high marks.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Traitez un seul sujet de composition. Vous devez baser votre réponse sur au moins deux des œuvres de la 3e partie que vous avez étudiées. Le cas échéant, vous pouvez inclure dans votre réponse une discussion sur une œuvre du même genre littéraire étudiée dans la 2e partie du programme. Les réponses qui ne sont pas basées sur au moins deux des œuvres de la 3e partie n'obtiendront pas une note élevée.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Elija un tema de redacción. Su respuesta deberá basarse en al menos dos de las obras estudiadas en la Parte 3. Se podrán hacer comentarios sobre una obra de la Parte 2 del mismo género, si fuera necesario. Las respuestas que no incluyan una discusión sobre al menos dos obras de la Parte 3 no recibirán notas altas.

***ከሚከተሉት በአንዱ ላይ ሀተታ ፃፍ(ፃፊ):: መልስህ በክፍል 3 ባጠናህቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ መመስረት አለበት:: በክፍል ሁለት ስር ከሚገኝ አንድ ተመሳሳይ የስነጽሁፍ ዘርፍ ማጣቀሻ ማስገባት ይፈቀዳል:: በክፍል 3 ባጠናህቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ ያልተመሰረተ መልስ ከፍተኛ ነጥብ አያስገኝም::***

**ድራማ**

**1.** ተከታዩን

(ሀ) በተውኔት፣ በተመልካቹና ተውኔቱ በሚያቀርበው አለም መካከል የሚቆም አንዳችም ነገር የለም:: በመሆኑም ተውኔት ምናባዊውን እውነታ በቀጥታ ለተመልካች ያቀርባል:: ያጠናሃቸውን ስራዎች ሁለት ቁልፍ የሆኑ ትእይንቶች በማወዳደር የዚህን ሃሳብ ትክክለኛነት አስረዳ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) እንደ ፀደይና መፀው ወቅቶች ሁሉ ትራጀዲና ኮመዲም በእኩል ደረጃ ጠቀሜታ ያላቸው የድራማ ክፍሎች ናቸው::ያጠናሃቸው ሁለት ድራማዎች በነዚህ ሁለት የድራማ ክፍሎች እንዲመደቡ የሚስችሉዋቸውን ገጽታዎቻቸውን በማወዳደር ይህንን ሃሳብ ግለጽ::

**ረጅም ልቦለድ**

**2.** ተከታዩን

(ሀ) የረጅም ልቦለድ ገፀባህርያት ሁለት ዐይነት ባህሪያትን ያንፀባርቃሉ ማለት ይቻላል:: ከሁለቱ አንዱ የግል ባህርያትን ማሳየት ሲሆን ሌላው የሰዎችን የጋራ የሆኑ ባህርያት ማንፀባረቅ ነው:: ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማነፃፀር ይህንን ሃሳብ ግለጽ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) ማንኛውም ልቦለድ የግዴታ የህይወትን አንድ አቅጣጫ ወይም ችግር ሊያሳይ ይገባል:: ባጠናሃቸው ሁለት ስራዎች ደራስያኑ ይህንን እንዴት እንዳቀረቡ አሳይ::

**ስነግጥም**

3. ተከታዩን

(ሀ) ገጣሚው በአንባብያን ዘንድ አልባሌ ለሚባሉ ወይም ብዙ ቦታ ለማያገኙ ነገሮች ያለውን ትኩረት በስራዎቹ ያሳያል:: ስራዎቻቸውን ያነበብካቸው ሁለት ገጣምያን በግጥሞቻቸው ይህንን እንደምን በሚገባ ለማሳየት እንደቻሉ አብራራ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) ስነግጥም መመዘን የሚገባው ታላላቅ ገጠመኞቻችንንና ፍላጎቶቻችንን በማሳየቱ ረገድ ባለው ከፍተኛ ሃይል ነው:: በግጥም በሚቀርበው ጉዳይና በአቀራረቡ መካከል ያለውን ዝምድና ያነበብካቸውን ግጥሞች በመጥቀስ አስረዳ::

**ዝርው (ከአጭርና ረጅም ልቦለድ ውጪ)**

4. ተከታዩን

(ሀ) የዝርው ጽሁፍ(ለምሳሌም ወግ) ፀሀፊዎች በአንባቢው ላይ ማሳደር የሚፈልጉትን ማንኛውም ተጽእኖ ለማሳደር ይችላሉ:::: ይህንን አረፍተ ነገር ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በመመርኮዝ ግለጽ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) የዝርው ጽሁፍ(ለምሳሌም ወግ) ንባብ ከሰዎች ጋር እንዳለን ግንኙነት ሁሉ ትኩረትንና የጽሁፉን ሀሳብ ለመገንዘብ ዝግጁነትን ይፈልጋል:: ያጠናሃቸውን ሶስት ስራዎች በመመርኮዝ ይህ ትኩረትና ዝግጁነት ለምን እንደሚያስፈልግ ግለጽ::

**አጭር ልቦለድ**

5. ተከታዩን

(ሀ) የአጭር ልቦለድ ታሪክ ታሪክ ነው የምንለው ስለአንድ የለውጥ ሂደት ስለሚያወራ ነው:: ይህ ለውጥ ባጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች ውስጥ እንደምን ቀረበ?

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) የአጭር ልቦለድ ምልልስ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የልቦለዱን ትልም(ፕሎት) ለማጎልበትና ገፀባህሪያቱም ከትልሙ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማሳየት ይረዳል:: ይህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር አስረዳ::

**ሁለገብ (አጠቃላይ)**

**6.** ከሚከተሉት አንዱን መርጠህ መልስ(ሽ)::

(ሀ) ስልት (ስታይል) ፀሀፊው በተለየ የራሱ መንገድ ነገሮችን የሚገልጽበት ዘዴ ነው:: ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በመጥቀስ ሀሳብህን ግለጽ::

ወይም

(ለ) የስነጽሁፍ ቃላት ምናባዊ ሰዎችንና ድርጊቶችን ከመፍጠር ሌላ ስሜትንና ሃሳብን በመግለጽ ያገለግላሉ:: በሁለት ስራዎች ምሳሌነት እነዚህን የቃላት አገልግሎቶች አብራራ::

ወይም

(ሐ) ስነጽሁፍ እኛ ከምናውቀው በላይ ሠፊ : ጥልቅና የተለያዩ የህይወት ገጽታዎችን እንድናይ ያደርገናል:: ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በመጥቀስ ሀሳብህን ግለጽ::

ወይም

(መ) ማንኛውም የስነጽሁፍ ስራ አንዱ መለያ ባህሪ ጭብጡ ምንም ሆነ ምን የሚያነሳውን ጉዳይ ኪነጥበባዊ ውበት አላብሶ ማቅረቡ ነው:: በሶስት ስራዎች ምሳሌነት በጭብጥና በስልት መካከል ያለውን ትስስር አሳይ::